# በመንዝና ጊሼ ሰዎች በራኃብ መሞታቸው ተገለጠ

በሰሜን ሸዋ በመንዝና ግጀ ልዩ ዞን በመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ውስጥ ብቻ አሥራ ዘጠኝ ሰዎች በራኃብ መሞታቸውን ጳጉሜ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ይፋ የወጣ አንድ ሠነድ ገለጠ።

በዚህም መሠረት በወረዳው በቀበሌ 12

ውስጥ ነዋሪ የነበሩ 1. ወ/ሮ ጥሩወቅር በየነ 2. አቶ ማሙዬ ዘነበ 3. አቶ ጋሻው በረደድ 4. አቶ ገረመው በጋሻው 5. ወ/ሮ በቀለች አይገፉና 6. ወ/ሮ የሺአመቤት ወንድምነህ የተባሉ ሰዎች በጥቂት ቀናት ውስጥ በተከታታይ በራኃብ አደጋ መሞታቸውን ሠነዱ አመልክቷል።

እንዲሁም በቀበሌ 14፤ 15ና 16 ውስጥ ነዋሪ የነበሩ 1. አቶ ጌታቸው መኩንን 2. አቶ ቸርነት ደርቤና አቶ ቸሩ አጋጅየለው የተባሉ ግለሰቦች በራኃብ ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በተዛመደ ሁኔታ 1. አቶ በለጠ መብራቴ 2. ወ/ሮ የሺ ጣሰው 3. አቶ ወልደኪዳን ባዩ 4. ወ/ሮ ሙሉአመቤት አሣልፍ 5. ወ/ሮ በለጡ ዳርጌ 6. አቶ ቸሬ መንገሻ 7. ወ/ሮ የብሬ ደነቀ 8. አቶ በለጥ ገበየሁ 9. አቶ ተስፋዬ ላቂና 10. ወ/ሮ ክበበ አሰፋ የተባሉ የመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ነዋሪዎች በራኃብ ምክንያት መሞተቸውን ተጠቃሹ ሠነድ አረጋግጧል።

ራኃቡ አሁንም ተስፋፍቶ የቀጠለ ሲሆን ብዙ የወረዳው ነዋሪዎች በሞት አፋፍ እንደሚገኙ ታውቃል።

EthioLion.com